# ግንቦት 7 ከውስጥ ተከፈለ
# በቃ እንዳለ ራሱ በቃ አለቀለት

ከአስተዋይ በቀለ

ግንቦት 7 የወረቀት ነብር የሆነ ቡፋ ነው ። አላቢላው ግንቦት 7 እንዲያው በከንቱ አንገቱን እንደ ዕብራውያን ሴቶች ለማግዘፍ ሞከረ እንጂ የትም እንደማይደርስና ይልቁንም እሳት ውስጥ እንደተወረወረ ጅማት አሮ እንደሚኮማተር የፖለቲካ ታዛቢዎች አበከረው ገምግመው ገና ድሮ በምስረታው ንጋት ላይ የተረዱት ሐቅ ነው ።

ይኸው ብዙ ሳይቆይ መለስና ፓትርያርኩን ተከትሎ ግንቦት 7 ከውስጥ ተደረመሰ _ተከፈለ። ሃሌ ሉያ እግዚአብሔር ታላቅ ነው የኢትጵያ አምላክ ።

ከትናንት እስከ ዛሬ ግንቦት 7ን አቅፈው ፣ አምነውና ደግፈው ሲያሸበሽቡና ሲያሸረግዱ የነበሩ ወገኖች፣ በቸሩ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ አምላክ መለኮታዊ እገዛ ነቅተው ተገንጥለው ወጥተው ይህው የእውነቱ ምስክር ሆነው አዲስ የፖለቲካ ድርጅታችንን እወቁልን እያሉ ነው።

*ነገር ግን በዚህ አጋጣ አንድ አብይ ነገር መገንዘብ ያስፈልጋል:: ይኸውም እውቅና ከተፈለገ ከኢትዮጵያ፣ ከሕዝቧና ከባንዲራዋ ጥቅሞች አንጻር እትብትን መቁረጥና ከግንቦት 7 በስምና በራእይ ሙሉ በሙሉ ተለይቶ መላቀቅንና በፖለቲካ ንስሓ እንደ በረዶ ነጥቶ መገኘትን ይጠይቃል:: በዚህ ላይ መዋለል ፣መዋዠቅና መንጀላጀል ካለ አልሸሹም ዞር አሉ ማለት ይሆንና ከፀረ_ ኢትዮጵያና ከዳቢሎሱ ግንቦት 7 ለይቶ ለማየት አይቻልም::*

ግንቦት 7 በውልና በውን ለኢትዮጵያ የቆመ አይደለም። ይህ ድርጅት በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነትና በአረንጓ _ቢጫ_ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ላይ ፅኑ አቋም የለውም ። ለማይደፈረው አገራችን፣ ለማይገሰሰው ዳር ድንበራችን ክብርና ከወያኔ ሙሉ በሙሉ ለማዳን ራእይና የቀረጠ አቋምም የለውም ። ከዚህ አገርን ከማዳን ይልቅ ከፀረ_ ኢትዮጵያ ገንጣዮችና ባንዳዎች ጋር መደራደርንና መቻቻልን ይመርጣል። እስከ አሁን ያሳየን ይህንኑ የጎደፈ ተግባር ነው።

ግንቦት 7 ከኢትዮጵያ ጠላት ከሻቢያ ጋር የገጠመ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል መሆኗን የካደ፣ ከሌሎች አገር ገንጣዮች ጋር የወገነ፣ ብሔራዊ ከሃዲዎችንና ሌሎችንም መሰሪ ልቅምቅሞችን ያቀፈ ፣ በሃሰት እንዲህ ነኝ እንዲያ ነኝ እያለ ገንዘብ የሚልጥ ኪስ አውላቂ የሆነና በጥቂት አምባገነን መሪወቹ ገመድ የተውተበተበ ቀይ ሙብራት የበራበትና ያለቀለት ድርምስ ነው ።

ግንቦት 7 ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ በተሰኙ ሽጋ ቃላቶች ቢያሸበርቅና መሪዎችም ዓላማችን ሥልጣን ለመያዝ አይደለም ቢሉም ፤ ድርጅቱ ሃሰትና ማጭበርበር የተሞላበት የድውይ አምባገነኖች አምባና መጋዘን ነው ። እነዚህ የድርጅቱ አምባገነን መሪዎች በትዕቢት የተነፉ የሥጋ ትቢያዎች እንጂ የፖለቲካ እውቀት፣ ብስለትና ሙያ ያላቸው ሰዎች አይደሉም ። በተለይም ግንባር ቀደም የሆኑት መሪዎች ለቅንጅት

መፍረስ ብሎም ለብዙ ሰዎች መሞት፣ መቁሰልና መታሰር፣ እንዲሁም የሕዝብን ተስፋ በማጨናገፍና የወያኔ ሰለባ  በማድረግ ተጠያቂ መሆናቸው ምንጊዜም የማይረሳና የማይቀር ነው ።

የዚህ ድርጅት አባል የሆናችሁ ሁሉ ልብ ግዙ ! ! የድርጅታችሁ ጽርስፎራ ተቀስፏል ። ከእንግዲህ በቃ አለቀ ። "ብርሌ ከተሰነጠቀ አይንም ዕቃ" ስለዚህ የግንቦት 7 መሪዎችን የፖለቲካ ኅብስት አድርጋችሁ የምታመልኩና ድርጅቱንም ወደ ኢትዮጵያ መጠጊያ አምባ ይሆነናል ብላችሁ የተጠጋችሁ ሁሉ ቶሎ ውጡና የኢትዮጵያን ሕዝብና አገር ወዳጁን ተቀላቀሉ ።

ድሮም ግንቦት ኀደሎና ሰላቢ ስለሆነ ግንቦት 7 ከሚለው ስያሜ ሙሉ በሙሉ አለመላቀቅ ኃላ የሚያመጣው መዘዝ መርዝ ነው ። ስለዚህ ለአገርና ለሕዝብ በሐቅ እንቆማለን የምትሉ ሁሉ አሁን በአንጃው የታቀፈውን ስም እርግፍ አርጎ ለመቀየር መታገል አለባችሁ ። አለበዚያ አልሸሹም ዞር አሉ ይሆንና የሚሸመተው የፖለቲካ ክሬዲቢሊቲ ያጣ ፌዝና ፉተታ ይሆናል ።

ድሮም ለኢትዮጵያ ያልሆነ የትም አይደርስም !

አገርና ሕዝብ ያሸንፋል !!